MARYLAND STATE DEPARTMENT OF
EDUCATION
EQUITY AND EXCELLENCE

2023



## የወላጅ ተከታታይ መረጃ
በ Maryland የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች፡-

## ተጓዳኝ መመሪያ ለ

# ተለዋጭ የትምህርት ማዕቀፍ



# መግቢያ

**የወላጅ ተከታታይ መረጃ በ Maryland ውስጥ በስቴት አቀፍ የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች ስርዓት ውስጥ ቤተሰቦችን ለመደገፍ የተነደፈ የሕትመት ስብስብ ነው።** በዚህ መጣጥፍ፣ ወደ ቁርጠኛ ባለሙያዎች ማህበረሰብ እንኳን ደህና መጡ ልንልዎት፣ እና የልጅዎን ስኬት ለመደገፍ እና ቤተሰብዎን ለመርዳት በፌደራል እና በስቴት ህግ በተፈጠረው ሂደት ውስጥ ልንመራዎ እንፈልጋለን።



# የማውጫ ሰንጠረዥ


ገጽ 4

**አማራጭ የትምህርት ማዕቀፍ ምንድን ነው?**

ገጽ 5

**አንድ ልጅ በአማራጭ የትምህርት ማዕቀፍ ውስጥ ለመሳተፍ ብቁ እንደሆነ የሚወሰነው እንዴት ነው?**

ገጽ 6

**በሂደቱ ውስጥ የወላጅ ስምምነት**

ገጽ 7

**የስምምነት ውሳኔዎችን ተከትሎ የሚመጣ ምርጫ እና ተጽዕኖ**

ገጽ 8

**በአማራጭ የትምህርት ማዕቀፍ ውስጥ ለሚሳተፉ ተማሪዎች የሚገኙ ውጤቶች**

ገጽ 9

**ለወላጆች የማረጋገጫ ዝርዝር**

ገጽ 10

**የቃላት መፍቻ**


ለበለጠ መረጃ በሚከተለው ይጎብኙን

**www.marylandpublicschools.org**



# ተለዋጭ **የትምህርት ማዕቀፍ ምንድን ነው?**

የልዩ ፍላጎት ትምህርት ዓላማ ሁሉም ብቁ የሆኑ አካል ጉዳተኛ ልጆች ልዩ ፍላጎቶቻቸውን የሚያሟላ እና ለቀጣይ ትምህርት፣ ሥራ እና የግል ኑሮ የሚያዘጋጃቸውን ነፃ ተገቢ የሕዝብ ትምህርት ወይም FAPE እንዲያገኙ ማድረግ ነው።

ሁሉም ተማሪዎች ተመሳሳይ የክፍል ደረጃ መስፈርቶች እንዲኖራቸው እና ከፍተኛ ተስፋዎችን እንዲያሟሉ ይጠበቃል፣ ይሁን እንጂ ሕጉ በጣም ጉልህ የሆነ የእውቀት( ኮግኒቲቭ) ጉድለት ያለባቸው ጥቂት ተማሪዎች ጥልቀት ያለው የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎት ቢያገኙም እንኳ ለሁሉም ተማሪዎች የሚተገበሩት መስፈርቶች ላይ ሊደርሱ እንደማይችሉ ይገነዘባል።

እነዚህ ተማሪዎች የተሻሻሉ መስፈርቶችን በመጠቀም ትምህርት እና ግምገማ ሊያስፈልጋቸው ይችላል። ይህ የትምህርት ቤት ሰራተኞች በአስፈላጊ የክፍል ደረጃ ክህሎቶች ላይ እንዲያተኩሩ እና የተጠናከረ፣ ቀጥተኛ የትምህርት አሰጣጥ እና ተደጋጋሚ ልምምድ እንዲኖር ያስችላል። የተለዋጭ ማዕቀፍን በመጠቀም የማስተማሪያ አስፈላጊ አካላት ከ Maryland ኰሌጅ እና የሙያ ዝግጁ ደረጃዎች ጋር የተጣጣሙ ቢሆኑም ተማሪው በክፍል ደረጃ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ከመግባቱ በፊት ቊልፍ ጽንሰ-ሀሳቦችን መማር እንዲችል ተለውጠዋል። የስቴት ምዘናዎች እንዲሁ የተማሪዎችን በክፍል ደረጃ መለኪያዎች ላይ በመገምገም የተለዩ ናቸው እና ሌሎች ተማሪዎች ሊመዘኑበት ከሚችለው አንፃር ውስብስብ አይደሉም።

> [የአንድ ልጅ] የትምህርት መርሃ ግብር ከሁኔታው አንጻር በተገቢው መንገድ ከፍተኛ ግምት ሊሰጠው የሚገባ መሆን አለበት....ግቦቹ ሊለያዩ ይችላሉ፣ ነገር ግን እያንዳንዱ ልጅ ፈታኝ የሆኑ አላማዎችን የማሳካት እድል ሊኖረው ይገባል።
>
> — Endrew F. v. Douglas County School Dist. _ U.S. _ (2017)

# አንድ ልጅ **በተለዋጭ የትምህርት ማዕቀፍ ውስጥ ለመሳተፍ** ብቁ የሚሆነው እንዴት ነው?

በተለዋጭ የትምህርት ማዕቀፍ ውስጥ ለመሳተፍ ብቁ ለመሆን የልጅዎ የግለሰባዊ ትምህርት መርሃ ግብር (IEP) ቡድን፣ እርስዎን ጨምሮ፣ ይህንን ውሳኔ በየዓመቱ ይወስናል። የIEP ቡድን ልጅዎ ጉልህ የሆነ የግንዛቤ ችግር ስላለበት በተለዋጭ ማዕቀፍ ውስጥ ለመሳተፍ ብቁ ሊሆን ይችላል የሚል ጥርጣሬ ካለው ቡድኑ “አባሪ ሀ” የተባለውን ሰነድ የ IEP አካል በማድረግ ያጠናቅቃል። ይህ ሰነድ የሚከተሉትን ይመለከታል፦

1. ተማሪው በእነዚህ ድጋፎች እንኳን ተማሪው አጠቃላይ መመዘኛዎችን መማር እንደማይችል የሚያሳይ በልዩ ሁኔታ የተነደፈ የማስተማር እና የአፈጻጸም መረጃን ያካተተ IEP አለው? እናም
2. ተማሪው ከፍተኛ የግንዛቤ (ኮግኒቲቭ) እክል አለበት? እናም
3. የተማሪው የትምህርት ይዘት ተማሪው እድገት እንዲያሳይ ከ Maryland ኮሌጅ እና ለሙያ ዝግጁነት ደረጃዎች በእንግሊዝኛ/ቋንቋ ጥበባት፣ በሂሳብ እና በቀጣዩ ትውልድ የሳይንስ ደረጃዎች ከክፍል ደረጃ ሥርዓተ ትምህርት ጋር በተጣጣመ መልኩ በከፍተኛ ሁኔታ ተስተካክሏል? እናም
4. ተማሪው በተጣጣመ እና በተስተካከለ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ሊለካ የሚችል ግኝቶችን ለማግኘት ሰፋ ያለ፣ ቀጥተኛ፣ ግለሰባዊ እና ተደጋጋሚ ትምህርት እና ከፍተኛ ድጋፍ ይፈልጋል?



# **በሂደቱ ውስጥ** የወላጅ ስምምነት

በ Maryland፣ በተሻሻለው ሥርዓተ ትምህርት እና በተለዋጭ የስቴት ምዘናዎች ላይ ለመሳተፍ የተለየ ስምምነት ያስፈልጋል፣ ስለዚህ ወላጆች ሁለት ጊዜ እንዲፈርሙ ይጠየቃሉ። ሁለቱም ውሳኔዎች - በሥርዓተ ትምህርቱ እና በምዘናው ውስጥ መሳተፍ - በየዓመቱ በተለምዶ በልጅዎ ዓመታዊ ግምገማ ስብሰባ ላይ ይደረጋሉ።

ወላጆች እነዚህ ሁለት የተለያዩ ውሳኔዎች መሆናቸውን መረዳት አለባቸው። የመጀመሪያው ውሳኔ፣ ልጅዎ በተሻሻሉት መስፈርቶች ውስጥ መሳተፍ አለመሳተፉ፣ ልጅዎ በየቀኑ የሚማረውን ነገር ይመለከታል። በእርስዎ ስምምነት፣ ልጅዎ አሁንም የክፍል ደረጃ መስፈርቶች "አስፈላጊ ክፍሎችን" መማር ይጠበቅበታል፣ ነገር ግን እነሱ ይሻሻላሉ። (ከዚህ በታች ያለውን ምሳሌ ይመልከቱ)።

ሁለተኛው ውሳኔ፣ ልጅዎ በተለዋጭ የስቴት ምዘናዎች ላይ እንዲሳተፍ ስምምነት መስጠት፣ እንዲሁ በየዓመቱ ይደረጋል።

ወላጆች በማንኛውም ጊዜ ከአንዱም ሆነ ከሁለቱም ውሳኔዎች ጋር በተያያዘ የሰጡትን ስምምነት የመሻር መብት አላቸው። አንድ ወላጅ እርግጠኛ ስላልሆኑ ወይም በሌላ ምክንያት ውሳኔ ካላደረጉ፣ የIEP ቡድን ውሳኔውን ከ15 የቀን መቁጠሪያ ቀናት በኋላ ተግባራዊ ያደርጋል።

| የ5ኛ ክፍል ደረጃ መስፈርት | ከ5ኛ ክፍል መስፈርት አስፈላጊ ክፍል |
|---|---|
| በጽሁፉ ውስጥ ባለው ልዩ መረጃ ላይ በመመስረት በታሪካዊ፣ ሳይንሳዊ ወይም ቴክኒካዊ ፅሁፍ ውስጥ በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ግለሰቦች፣ ክስተቶች፣ ሃሳቦች ወይም ጽንሰ-ሀሳቦች መካከል ያለውን ግንኙነት ወይም መስተጋብር ማብራራት። | በአንድ ጽሑፍ ውስጥ ሁለት ግለሰቦችን፣ ክስተቶችን ወይም ሃሳቦችን ማወዳደር |
| አስፈላጊ ጥያቄ፦ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ የዩናይትድ ስቴትስ ዜጎችን የሚጠብቀው እንዴት ነው? ተማሪው የተለያየ ፍላጎት ያላቸው ግለሰቦች ለፌዴራሊስት እና ፀረ-ፌዴራሊስት አመለካከቶች መፈጠር እንዴት አስተዋፅዖ እንደሚያበረክቱ ይተነትናል፤<br><br>የሜሪላንድ የመብቶች አዋጅ በ Daniel Carroll፣ Luther Martin፣ እና John Francis Mercer መካከል በማጽደቅ ላይ በተደረገው ክርክር ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያሳድር መገምገም፤<br><br>የመጀመሪያዎቹን አስር የሕገ መንግሥቱ ማሻሻያዎች ዓላማ እና አስፈላጊነት መለየት፤<br><br>ማሻሻያዎቹ በአሁኑ ጊዜ በ Maryland እና በሀገሪቱ ውስጥ እንዴት እንደሚተገበሩ መመርመር። | አስፈላጊ ጥያቄ፦ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ የዩናይትድ ስቴትስ ዜጎችን የሚጠብቀው እንዴት ነው? ተማሪዎች የአሜሪካ ሕገ መንግሥት የመጀመሪያዎቹን አስር ማሻሻያዎች ያነባሉ እናም በአሁኑ ጊዜ በ Maryland እና በሀገሪቱ ውስጥ እንዴት እንደሚተገበሩ ይመረምራሉ። |



# **የወላጅ ስምምነትን ተከትሎ** የሚመጣ ምርጫዎች እና ተጽዕኖ

አንድ ወላጅ ልጃቸው በተለዋጭ የትምህርት ማዕቀፍ ውስጥ እንዲሳተፍ ፈቃድ መስጠት አለባቸው። አይሆንም ካሉ ባልተሻሻሉ የክፍል ደረጃ መስፈርቶች በ IEP ውስጥ በተገለጸው መሰረት ከሚሰጡ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ድጋፎች እና አገልግሎቶች ጋር ልጃቸው የአጠቃላይ ትምህርት መርሃ ግብርን ማወቅ ይጠበቅበታል። እንደ አጠቃላይ ትምህርት ተማሪ ሆነው በትምህርት ቤትዎ ስርዓት ፖሊሲ መሰረት ይመዘኑ እና ደረጃ ይሰጣቸዋል። እንዲሁም በአጠቃላይ የስቴት ምዘናዎች የሚፈቀዱ ማመቻቸቶች እና ድጋፎችን በመጠቀም ይመዘናሉ።

ልጅዎ በተሻሻሉት የትምህርት ደረጃዎች እና በተለዋጭ የስቴት ምዘናዎች ላይ እንዲሳተፍ የተለየ ስምምነት ያስፈልጋል። ሁለቱ ውሳኔዎች ሊጣጣሙ ቢችሉም፣ ወላጆች ለአንዱ ሳይሆን ለሌላው፣ ለሁለቱም፣ ወይም ለአንዱም ፈቃድ ለመስጠት ወይም ላለመስጠት ሊመርጡ ይችላሉ። የ IEP ቡድኑ አባሪ ሀን ቢያጠናቅቅ እና አንድ ልጅ በተለዋጭ የትምህርት ማዕቀፍ ውስጥ ለመሳተፍ ብቁ እንደሆነ ከወሰነ፣ ወላጅ አሁንም ይህን እንዲያደርጉ ፈቃድ ላለመስጠት ሊወስኑ ይችላሉ። ትምህርት ቤቱ ለልጁ ነፃ ተገቢ የሕዝብ ትምህርት (FAPE) የመስጠት ግዴታውን ይቀጥላል። ትምህርት ቤቱ ለልጁ FAPE ለመስጠት ብቸኛው መንገድ ተማሪው በተለዋጭ ማዕቀፍ ውስጥ መሳተፉ እንደሆነ ከወሰነ፣ አለመግባባቱን ለመፍታት መደበኛ የግጭት አፈታት ሂደቶችን ሽምግልና እና/ወይም የፍትህ ሂደት ችሎት መጠቀም አለባቸው። ይህ በፌደራል እና በስቴት ሕግ የሚፈለግ ነው።

ወላጆች ስምምነታቸውን ለመስጠት ወይም ላለመስጠት በሚወስኑበት ጊዜ የሚከተሉትን ነገሮች ማስታወስ ይኖርባቸዋል፦

- የተሳትፎ ውሳኔው በየዓመቱ ይከናወናል፤
- በማንኛውም ጊዜ ስምምነትን መሻር ይችላሉ፤
- የተሳትፎ ውሳኔው ምደባን፣ የትምህርት አካባቢን፣ ትምህርት ቤትን፣ ወይም ፕሮግራምን አይወስንም፤
- ልጁ በተለዋጭ ማዕቀፍ ውስጥ ረዘም ላለ ጊዜ በተሳተፈ ቁጥር፣ ዲፕሎማ የማግኘት ዕድሉ ይቀንሳል፤ ቢሆንም፤
- ከተቻለ ልጅዎ አሁንም ቢሆን ዲፕሎማ ለማግኘት ሊሞክር ይችላል።

# በአማራጭ የትምህርት ማዕቀፍ ውስጥ
## ለሚሳተፉ ተማሪዎች የሚገኙ ውጤቶች



ሁሉም ተማሪዎች ልዩ ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት የተነደፈ ጥብቅ ትምህርት እንዲኖራቸው ይጠበቃል። በተለዋጭ የትምህርት ማዕቀፍ ውስጥ መሳተፍ የልጅዎን የተለየ ምደባ አይወስንም። እነዚህ ፍጹም የተለዩ ውሳኔዎች ናቸው እና የአካል ጉዳተኞች ትምህርት ህግ (IDEA) ግዴታ ሁሉም ተማሪዎች በተቻለ መጠን የአካል ጉዳተኛ ካልሆኑ እኩዮቻቸው ጋር እንዲማሩ ነው። ይህ ትእዛዝ ከፍተኛ የእውቀት( ኮግኒቲቭ) እክል ላላቸው ተማሪዎች እኩል ይሠራል። የልጅዎ ግለሰባዊ ፍላጐቶች ከጠቅላላ ትምህርት ክፍል ውጭ ትምህርት እንዲሰጠው የሚጠይቁ ካልሆነ በስተቀር፣ በተለዋጭ የትምህርት ማዕቀፍ ውስጥ መሳተፍ በልዩ ፕሮግራም፣ ክፍል ወይም ትምህርት ቤት እንዲማር አይጠይቅም።

ወላጆች ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጀምሮ፣ ልጃቸው በተለዋጭ ማዕቀፍ ውስጥ ረዘም ላለ ጊዜ ሲሳተፍ፣ ወይም በሁለቱም የክፍል ትምህርት እና የስቴት ምዘና፣ ለተማሪው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንደደረሱ ዲፕሎማቸውን ለማግኘት የሚያስፈልጉትን ክሬዲቶች ለማግኘት እና የስቴት ምዘናዎችን ለማለፍ የሚያስፈልጉ  የክፍል ደረጃ የስርዓተ ትምህርት ደረጃዎችን መማር እና በአጠቃላይ በትምህርቱ መገምገም የበለጠ አስቸጋሪ እንደሚሆን ወላጆች መረዳት አለባቸው።  ይሁን እንጂ፣ በተለዋጭ የትምህርት ማዕቀፍ ውስጥ የሚሳተፍ ማንኛውም ተማሪ ዲፕሎማውን ለማግኘት ከመሞከር ተስፋ ሊቆርጥ አይገባም።

ዲፕሎማቸውን ማግኘት የማይችሉ ተማሪዎች የ Maryland የፕሮግራም ማጠናቀቂያ የምስክር ወረቀት ያገኛሉ። በከፍተኛ ተስፋ እና እቅዶች፣ ትምህርታቸው በነፃነት እና በስኬት ወደሚኖሩበት የሙያ እና የማህበረሰብ ሽግግር ያዘጋጃቸዋል።



# **ለወላጆች** የማረጋገጫ ዝርዝር

## ለሚከተሉት ጥያቄዎች “አዎ” ብለው መመለስ ይችላሉ?

ካልሆነ፣ ለልጅዎ ጉዳይ አስተዳዳሪ፣ ለልጅዎ አስተዳዳሪ፣ በትምህርት ቤትዎ ውስጥ ላለው የቤተሰብ ድጋፍ አስተባባሪ፣ ወይም በ MSDE ላለው የቤተሰብ ድጋፍ ቡድን ይደውሉ።

### ተለዋጭ የትምህርት ማዕቀፍ

- ❍ አንድ ተማሪ በ Maryland ውስጥ በተለዋጭ የትምህርት ማዕቀፍ ውስጥ ለመሳተፍ ብቁ መሆኑ እንዴት እንደሚወሰን ተረድቻለሁ?
- ❍ ስምምነት የመስጠት መብቴ እና የእነዚህ ውሳኔዎች ውጤት ምን እንደሆነ ተረድቻለሁ?
- ❍ በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ያለኝን ሚና ተረድቻለሁ?
- ❍ ለልጄ ትምህርት እቅድ በማውጣት ረገድ የቤተሰቤን  ስጋቶች እና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች ማካፈል እንደምችል አውቃለሁ?
- ❍ ልጄ በተለዋጭ ማዕቀፍ ውስጥ እንዲሳተፍ በየዓመቱ የጽሁፍ ስምምነት መስጠት እንዳለብኝ ተረድቻለሁ?
- ❍ በውሳኔዎቼ ላይ በመመርኮዝ የትምህርት ቤት ስርዓቱ ሊወስዳቸው የሚችላቸውን እርምጃዎች ተረድቻለሁ?
- ❍ የልጄን በተለዋጭ ማዕቀፍ ውስጥ መሳተፍን በሚመለከት ውሳኔዎቼ ሊያስከትሉ የሚችሉትን ውጤት ተረድቻለሁ?
- ❍ ልጄ በተለዋጭ የትምህርት ማዕቀፍ ውስጥ ለመሳተፍ ብቁ ሆኖ ከተገኘ፣ ለምን እንደሆነ ተረድቻለሁ?

# የሁለተኛ ደረጃ ሽግግር
# **የቃላት መፍቻ**

**ተለዋጭ የትምህርት ማዕቀፍ**
በጣም ጉልህ የሆነ የግንዛቤ ችግር ላለባቸው ተማሪዎች የታሰበን ትምህርት እና ምዘና ያካትታል።

**የ Maryland ኮሌጅ እና የሙያ ዝግጁነት መስፈርቶች (MCCRS)**
ለሁሉም ተማሪዎች ግልጽ፣ ከፍተኛ ጥራት ያለው፣ የትምህርት ደረጃዎችን የሚያቀርቡ የስቴት አቀፍ የክፍል ደረጃ መስፈርቶች።

**ጉልህ የሆነ የግንዛቤ ጉድለት**
የተማሪን የመላመድ፣ የአፈጻጸም፣ የእውቀት (ኮግኒቲቭ)፣ የመማር መገለጫ የሚያንፀባርቅ የውሂብ ስብስብ።

**አስፈላጊ ክፍሎች**
ከ MCCRS የተገኙ እና የተጣጣሙ ሁሉም ተማሪዎች ከፍተኛ የአካዳሚክ ውጤቶችን እንዳገኙ ለማረጋገጥ የሚውሉ የክፍል ደረጃ የስኬት መመዘኛዎች።

**አባሪ ሀ**
ተማሪው በተለዋጭ የትምህርት ማዕቀፍ ውስጥ ለመሳተፍ መስፈርቱን የሚያሟላ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለመወሰን ቡድኑ በየዓመቱ የሚሞላው የIEP ቅጽ።

**MCAP (የ Maryland አጠቃላይ ምዘና ፕሮግራም)**
በ Maryland ኮሌጅ እና ለሙያ ዝግጁነት ደረጃዎች የተማሪ እድገትን በተመለከተ ለአስተማሪዎች፣ ለወላጆች እና ለህዝብ መረጃ የሚሰጥ የስቴት ምዘና ፕሮግራም።



**የ MARYLAND ስቴት የትምህርት መምሪያ**

**Mohammed Choudhury**
የስቴቱ የትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ

**Dr. Deann Collins**
የማስተማር እና መማር ቢሮ ምክትል የበላይ ተቆጣጣሪ

**Clarence C. Crawford**
የ Maryland ስቴት የትምህርት ቦርድ፣ ፕሬዝዳንት

**Wes Moore**
አስተዳዳሪ

© 2023 የ Maryland ስቴት የትምህርት መምሪያ
ይህ ህትመት የተዘጋጀው በ Maryland ስቴት የትምህርት መምሪያ፤ የቅድመ ጣልቃ ገብነት ክፍል እና የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች ከዩናይትድ ስቴትስ የትምህርት መምሪያ፤ የገንዘብ ድጋፍ #H393A090124A፤ የልዩ ፍላጎት ትምህርት የገንዘብ ድጋፍ ለህፃናት እና ቤተሰቦች “የማገገሚያ የገንዘብ ድጋፎች” በ PL 105-17/111-5 መሰረት የአካል ጉዳተኛ ግለሰቦች የትምህርት ህግ/የአሜሪካ ማገገሚያ እና መልሶ ማልማት ህግ በተገኘ ገንዘብ ድጋፍ ነው። የ Maryland ስቴት የትምህርት መምሪያ፤ የቅድሚያ ጣልቃገብነት ክፍል እና የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች፤ ለ Maryland ሕፃናት እና ታዳጊዎች መርሃ-ግብር መሪ ወኪል ድርጅት ነው፤ በስቴት እና በአካባቢ ኤጀንሲዎች እና ድርጅቶች የተቀናጁ የስቴት አቀፍ የአገልግሎት መርሃ-ግብሮች እና ድጋፎች። በዚህ ህትመት ውስጥ ያለውን መረጃ የሚያባዙ ወይም የሚያጋሩ ተጠቃሚዎች ለ Maryland ስቴት የትምህርት መምሪያ፣ የቅድመ ጣልቃ ገብነት እና የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች ክፍል፣ Dr. Deann Collins፤ የማስተማር እና ትምህርት ቢሮ ምክትል የበላይ ተቆጣጣሪ እውቅና መስጠት አለባቸው



MARYLAND STATE DEPARTMENT OF
EDUCATION
EQUITY AND EXCELLENCE

410-767-0100

www.marylandpublicschools.org

200 West Baltimore Street
Baltimore, MD 21201-2595